Arlington Public Schools

ARLINGTON VIRGINIA Public Health

# ወደ 12ኛ ክፍል ለመግባት ስለሚያስፈልገው ክትባት ጠቃሚ መረጃ

**በቨርጂኒያ ደንብ [§ 22.1-271.2] መሰረት በቨርጂኒያ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች በሙሉ የ MenACWY (ሜኒንጎኮካል) ማበረታቻ ክትባት 12ኛ ክፍል ከመግባታቸው በፊት መከተብ ይኖርባቸዋል**

*የማኒንጎኮካል መረጃ:*

- የ MenACWY (ሜኒንጎኮካል) ክትባቱ ከማጅራት ገትር በሽታ ጥበቃን የሚሰጥና ያልተለመደ ነገር ግን በባክቴሪያ የሚመጣ ከባድና አልፎ ተርፎ ለህልፈት ወደሚዳርግ ኢንፌክሽን ሊመራ ይችላል፡፡
- በተለይ ከ16 እስከ 23 አመት የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ የሚገኙ ወጣቶችና አዋቂዎች ለአደጋ ተጋላጭ ናቸው፡፡
- ምንም እንኳን እርስዎ/ተማሪዎ በጉርምስና እድሜ ክልል ላይ ባሉ ጊዜ የቀድሞ መጠን (ዶዝ) የወሰዱ ቢሆንም በአስራዎቹ እድሜ ላይ የሚገኙ ወጣቶች ከፍተኛ አደጋ በሚደርስባቸው ዕድሜዎች ላይ የሚገኙ በመሆናቸው ጥበቃን ለመስጠት በ16 አመታቸው የመከላከያ መጠን የሚያስፈልጋቸው ሲሆን ለዚህም ምክንያቱ ጥበቃ በጊዜ ሂደት እየቀነሰ የሚሄድ በመሆኑ ነው፡፡

*አስፈላጊ የሆኑ ዝርዝሮች:*

- ለእርስዎ/ለተማሪዎ የ MenACWY (ሜኒንጎኮካል) ማበረታቻ ክትባት **በ16ኛ የልደት ቀን** ወይም **በኋላ ከተሰጠዎ** (ወይም በህክምና ወይም በሃይማኖት ምክንያት ነጻ የመሆን ማረጋገጫ) የ 12ኛ ክፍል ከመጀመሩ በፊት ለትምህርት ቤት ክሊኒክ ማቅረብ ይኖርብዎታል፡፡
- **ለ2023-2024 የትምህርት ዘመን በአካል ትምህርት ቤት ተገኝቶ ለመከታተል ወይም እንቅስቃሴዎች ላይ ለመሳተፍ የእርስዎ/የእርስዎ ተማሪ የ MenACWY ሰነድ ወቅታዊ መሆን <u>አለበት</u>**፡፡

*እርስዎ/ተማሪዎ የ MenACWY ክትባት የት ማግኘት ይችላሉ?*

የ Tdap፣ MenACWY እና HPV ክትባቶችን ለመከተብ ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ የትኛው ለእርስዎ/ለእርስዎ ተማሪ የተሻለ እንደሆነ ለመወሰን [የትምህርት ቤትዎን የህዝብ ጤና ነርስ] ያነጋግሩ፡

- **ከተማሪዎ የመጀመሪያ ደረጃ ሕክምና ሰጪ**
  - ይህ አስፈላጊ የሆነው ክትባት በመድህን ዋስትና እቅዶች ሽፋን ያገኛል፡፡ ወደ ትምህርት ቤት የመመለስ ጥድፊያን ለማስቀረት እንዲቻል አሁኑኑ ቀጠሮ ይያዙ!
- **በ 2100 Washington Blvd ከሚገኘው የአርሊንግተን ካውንቲ የክትባት ክሊኒክ**
  - እንደ MenACWY (Meningococcal) ያሉ አስፈላጊ የሆኑ ክትባቶች ያለ ምንም ክፍያ የሚሰጡ ሲሆን ሌሎች የሚመከሩ ክትባቶች ክፍያን የሚያካትቱ ሊሆኑ ይችላሉ (ድረገጹን ይመልከቱ)
  - የስራ ቀናትና ሰአታት እዚህ ይገኛሉ፡ [የክትባት ክሊኒክ - የአርሊንግተን ካውንቲ ይፋዊ ድረገጽ (arlingtonva.us)]፡፡ ቀጠሮ መያዝ የሚያስፈልግ ሲሆን የጥበቃ ጊዜም ሊለያይ ይችላል
- **ከለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትዎ የጤና ክሊኒክ**
  - የትምህርት ቤትዎ [የጤና ክሊኒክ] በዚህ የጸደይ ወቅት መጨረሻ ላይ ለ MenACWY ክትባት ትምህርት ቤትን መሰረት ያደረገ የክትባት እድሎችን ያቀርባል
  - እነዚህን ክትባቶች በትምህርት ቤት ክሊኒክ ለመከተብ ምንም አይነት ክፍያ የማይፈጸም ሲሆን ነገር ነገር ግን ብቁነትና የመድህን ዋስትና ሁኔታ እንደ የግዴታ የስምምነት ሂደት አካል ይታያሉ፡፡
  - በየትኛውም አይነት ምክንያት ክትባቱ በትምህርት ቤት መሰጠት የማይቻል ከሆነ ተማሪው ሁሉንም የትምህርት ቤት መግቢያ የክትባት መስፈርቶችን ማሟላቱን ማረጋገጥ የወላጅ/አሳዳጊ ሃላፊነት ነው፡፡

**የአሁኑን የቨርጂኒያ ደንብና ለተደጋጋሚ ጥያቄዎችን እዝን ጨምሮ ተጨማሪ መረጃ በቨርጂኒያ የጤና መምሪያ ድረገጽ፡ [የትምህርት ቤት መስፈርቶች - ክትባት (virginia.gov)] ማግኘት ይችላሉ፡፡ ማንኛውም ጥያቄ የሚኖርዎ ከሆነ እባክዎን የትምህርት ቤቱን [የህዝብ ጤና ነርስ] ያግኙ፡፡**